ቅጽ 4 ቁጥር 3

ዜና መጽሔት
ጥር 2014 ዓ.ም

# ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
# Tourism training institute

since1969

## የኢንስቲትዩቱ የስድስት ወር ዕቅድ አፈፃፀም ተገመገመ።

ጥር 15/2014 ዓ.ም






የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ የስድስት ወር ዕቅድ አፈፃፀም የተቋሙ አመራሮች፣ መምህራንና ሰራተኞች በተገኙበት ተገምግሟል።

ኢንስቲትዩቱ ከመደበኛ የማሰልጠን፣ የማማከርና የምርምር ሥራዎች እና ከማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ባሻገር በስድስት ወር አፈፃፀሙ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸው የተገለጸ ሲሆን በተለይም በሲዳማ ክልል የዓለም ቱሪዝም ቀን መከበርን አስመልክቶ የክልሉን 31 ዓይነት ባህላዊ ምግብ ሳይንሳዊ በሆነ ደረጃ በማውጣት የተሰራው ለሆቴሎች በሚቀርብ ሜኑ ማዘጋጀት መቻሉ፤ የክልሉን የቱሪስት ቆይታ ማራዘም የሚያስችል ቱር ማፒንግ እና የጥቅል ጉዞ መዘጋጀቱ፤

በክልሉ ያሉ የአስጎብኝ ድርጅቶች እና የሆቴል ማናጀሮች የማነቃቂያ ስልጠና መሰጠቱ፣ የሸገር ፕሮጀክት የወንዞች ዳር ልማት ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ጋር የተሰሩ ሥራዎች ተቋሙን ከፍ ባለደረጃ ማስተዋወቃቸው ፣ ከተለያዩ ተቋማት ጋር የተሰሩ የአጫጭር ስልጠናዎች ፣ ለመምህራን እና ለሰልጣኞች የተሰጡ የማነቃቂያ ሥልጠና፤ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ የነበረው ከፍተኛ አስተዋጽኦ፤ በዘርፉ ለክልሎች የተሰጠው ሥልጠና በጥንካሬ የታዩ ናቸው።

በሌላም በኩል ተቋሙ ከዕቅድ አንፃር ያልተከናወኑ ሥራዎች አለመከናወናቸው በድክመት ታይቷል።

***በኮሙኒኬሽን ጉዳዮች የተዘጋጀ***

*ጥር 2014 ዓ.ም*

***f .....TTI.edu.et***

ቅጽ 4 ቁጥር 3

ዜና መጽሔት
ጥር 2014 ዓ.ም

# ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
# Tourism training institute

## ተቋማዊ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ተሰጠ።









ተቋማዊ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች ተሰጠ።
ጥር 15/2014ዓ.ም
=============================
የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለመምህራን እና ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ሥልጠና በተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ተሰጠ።
ኢንስቲትዩቱ በተጨማሪም የስድስት ወር ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ እና የተቋማዊ የተገልጋይ እርካታ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት ቀርቦ ውይይትም ተካሂዷል።
ሥልጠናው ደንበኛን በምን መልኩ ማስተናገድ እንደሚገባንና ጤናማ የእርስ በርስ ግንኙነት ለጤናማ የሥራ ላይ እንቅስቃሴን ያለውን ጠቀሜታ የሚያሳይ እና አነቃቂ ነው።
ተቋሙ ከሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል ከመስከረም 24 ዓ.ም በአዲስ ምዕራፍ የመንግስት ምስረታ በኋላ ወደ ቀድሞው ስያሜ ወደ ኢንስቲትዩት ያደገ ወደፊት በዘርፉ ካለው የረጅም ጊዜ የሥልጠና ልምድ ተጠቅሞ ለአገሪቱ የቱሪዝም ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ የሠለጠነ ባለሙያ የሚያፈራ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም እንዲሆን እየተሰራ መሆኑ ተገልጸዋል።





ከ200 በላይ ለሆኑ ሥራ አጥ
ወጣቶች በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፍ ስልጠና ተሰጠ።
ቱ ማ ኢ ጥር 6/2014 ዓ.ም
======================



በአዲስ አበባ ከተማ ካሉት ክፍለ ከተሞች መካከል ከሰባቱ የተወጣጡ ከ200 በላይ ሥራ አጥ ወጣቶች በቱሪዝምና በሆቴል ዘርፍ የኢንተርፕሪነር ሽፕ ስልጠና በተቋማችን መምህራን ስልጠና ተሰጥቷል።
ስልጠናው በአዲስ አበባ ከተማ ሜጋ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥር በUNDP ድጋፍና በኢንስቲትዩቱ የማማከር ተግባር አንጻር ለአምስት ቀን የቆየ መሆኑን የተቋማችን ምርምርና ማማከር ዳይሬክቶሬት አቶ ማዘንጊያ ሽመልስ ገልጸዋል።
ስለልጠናውን አስመልክቶ በስልጠናው የተሳተፉት ወጣቶች እንደገለጹት ስልጠናው በሆቴልም ሆነ በቱሪዝም በሀገራችን ያሉትን ሀብቶች እንዴት መጠቀም እንዳለብንና ቀጣይ ወደ ሥራ ዓለም ስንገባ የተሻለ ዕውቀት እንዲኖር ያደረገ ነው በማለት ሀሳባቸውን ገልጸዋል።
ሰልጣኞቹ በሙያው ባለቤት በሆኑ መምህራን ስልጠና መውሰዳቸው ይበልጥ የሚያበረታታ መሆኑን በመግለጽ ቀጣይነት ባለው መልኩ ስልጠና በማግኘት ወደ ሥራ ሲገባም ድጋፍ መለየት እንደሌለበት ሰልጣኞች ሀሳብ ሰጥተዋል።



ለሥራ አጥ ከሚሰጠው ስልጠና ጎን ለጎን ከሰባቱ ክፍለ ከተሞች ለተወጣጡ ባለሙያዎችና ቡድን መሪዎች ስለፕሮጀክቱ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱን የተቋማችን አካዳሚክ ዲን አቶ አብርሃም ለገሠ ተናግረዋል።
ስልጠናው ፕሮጀክቱ የሚያካልላቸው ከሰባቱ ክፍለ ከተሞች የተወጣጡ ከሃያ ለማይበልጡ ባለሙያዎችና ቡድን መሪዎች ስለፕሮጀክቱ ማስተዋወቅ እና ዓላማውንም ተረድተው ወደ ሥራ እንዲገቡ የሚያደርግ ነው ብለዋል።
ፕሮጀክቱ የወንዝ ዳርቻን በማልማት ለሴቶችና ወጣቶች ምቹ የሥራ ዕድል በመፍጠር አዲስ አበባ ከተማን ዕድገት ማሻሻል እንደሆነ አካዳሚክ ዲኑ ገልጸዋል።

ጥሩ ጽሁፍ ለመጻፍ ጥሩ አንባቢ መሆን አለብን" ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ






**ጥሩ ጽሁፍ ለመጻፍ ጥሩ አንባቢ መሆን አለብን"**
**ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ**
**ቱ .ማ .ኢ. ታህሳስ 24/2014 ዓ ም**

ለሁለት ቀን በኢትዮጵያ ምርምር ስራዎች ያሉበት ደረጃና ጠቃሚ የምርምር ጽሁፍ እንዴት መስራት እንደሚቻል ለቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት መምህራን ስልጠና ተሰጠ።
ስልጠናውን የሰጡት ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ ጥሩ ጸሐፊ ለመሆን ጥሩ አንባቢ መሆን እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። አንድ የምርምር ስራ የብዙ ሰዎች ሀሳብ ከተጨመረበት የተሻለ እንደሆነና ጥሩ ምርምር ምን ምን ማሟላት እንዳለበት ሰፊ ስልጠና ሰጥተዋል።
ፕሮፌሰር አፈወርቅ በነበራቸው ዓለም አቀፍ ተሞክሮ በርካታ የጥናት ወረቀቶችን ለማሳተም መቻላቸውን ገልጸው ነገር ግን እዚህ ለመድረስ በርካታ ውጣ ውረዶችን እንዳሳለፉ ልምዳቸውን ጭምር አካፍለዋል።
መምህራኑም በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሰሩትን አምስት የምርምር ሥራዎች አቅርበው ከስልጠናው ጋር በማያያዝ ጥሩ ውይይት ተካሂዶበታል።
በስልጠናው የተቋሙ የበላይ አመራሮች፣ የማኔጅመንት አባላትና መምህራን ተገኝተዋል።
ሰልጣኞቹ ቀጣይ ለሚኖሩ ሥራዎች ተቋንሙንም ሀገርንም በዘርፉ ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ የምርምር ሥራዎች መሥራት የሚያስችል አቅም መፈጠሩን ተናግረዋል።



# የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትና የኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት አመራርና ሰራተኞች በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት አደረጉ።





**የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትና የኢንተርፕርነርሺፕ ልማት ኢንስቲትዩት አመራርና ሰራተኞች በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት አደረጉ።**




**ቱ.ማ.ኢ ጥር 5/2014 ዓ.ም**

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትና የኢንተርፕርነር ልማት ኢንስቲትዩት አመራርና ሰራተኞች የድህረ ጦርነት መዛነፎችና እርምቶች "በሚል ርዕስ በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ለሁለት ቀናት ውይይት አካሂደዋል::
በዚህም በኢትዮጵያውያን አሸናፊነት የተጠናቀቀው የዘመቻ ህብረ ብሄራዊ አንድነት የመጀመሪያ ምዕራፍ በሌሎች ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ድሎች በሚጠናከርባቸው አቅጣጫዎች ላይ መክረዋል።
የተቋማችን የበላይ አመራሮች እንደገለጹት በጦርነቱ የተጎዳውን ሀገራዊ ኢኮኖሚ የማነቃነቅና በወራሪው ሃይል የከፋ ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች መልሶ መገንባት ሌላው ሀገራዊ ድል የምናስመዘግብበት የዘመቻ ምዕራፍ መሆን አለበት ብለዋል።
በውይይቱ የተገኙት የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ አሰግድ ጌታቸው በሰጡት ማብራሪያ አካታችና አሳታፊ ሀገራዊ የምክክር መድረክ በማካሄድ በሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ መግባባት ላይ ለመድረስ እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል።
ይህን ለመፈፀም የሚያስችሉ ተጨባጭ ዕርምጃዎችም በመንግስት በኩል እየተወሰዱ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።
ከዘመቻ ህብረ ብሄራዊ አንድነት ድሎች በኋላ በሀገር ደረጃ እየተወሰዱ ያሉ ውሳኔዎችና እርምጃዎች ዘላቂ ሀገራዊ ጥቅምን ታሳቢ ያደረጉ፣የተመዘገቡ ድሎቻችንን የሚያጎለብቱና በተለይ ከምዕራቡ ዓለም የሚደርስብንን ያልተገባ ጫና የሚያለዝቡ መሆናቸውም በውይይቱ ተነስቷል።









## በሆቴልና ቱሪዝም ሥልጠና ዘርፍ በስምንት የሙያ ደረጃዎች ማሻሻያ ተደረገ ።

ቱ. ማ. ኢ ታህሳስ 21/2014 ዓ ም

በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት እና በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ የጋራ ትብብር በሆቴልና ቱሪዝም ሥልጠና ዘርፍ በስምንት የሙያ ደረጃዎች ማሻሻያ ተደረገ።

ፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ቦርድ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ እንደገለጹት ይህን የሙያ ደረጃ ማሻሻያ ለመሥራት የሰጣችሁት ጊዜ፣ ጉልበት እና እውቀት በመልካም መሬት ላይ እንደወደቀች ፍሬ ናት ብለዋል።

ይህም የደረጃ ማሻሻያ በሚፈለገው መልክ ተዘጋጅቶ በሚጸድቅበት ጊዜ ለሀገራችሁ መልካም ሥራ እንደሰራችሁ ይታወቃችኋል።

ስለሆነም እስኪጸድቅ ድረስ ይጠቅማል የምትሉትን ሀሳብ እየጨመራችሁ ልታዳብሩት ይገባል በማለት ለሰሩት ሥራ አመስግነዋል።

የኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራሮች ተገኝተው ለአጥኚዎችና ለባለድርሻ አካላት ውድ ጊዜያችውን ሰውተው ሙያዊ አስተዋጽኦ ስላበረከቱ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ኢንዱስትሪ ሞቢላይዜሽን ፣ ሙያ ደረጃና ብቃት ምዘና ዳይሬክተር ወ/ሮ ንግስት መላኩ እንደገለፁት የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ሙያ ማሻሻያ ከዛሬ አስር ዓመት በፊት በተሰራበት እስከ አሁን እየተሰራ በመሆኑ ብዙ ችግሮች ያሉበት በመሆኑ ይህን ችግር የሚፈታ ማሻሻያ ይሰራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

በዚህ የሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር የዘርፉ ባለድርሻ አካላት የተሳተፉ ሲሆን ማሻሻያ የሚደረግባቸው የሙያ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው

* food & Beverage service የምግብ እና መጠጥ መስተንግዶ
* food & Beverage control የምግብና መጠጥ ቁጥጥር
* Housekeeping laundry service የቤት አያያዝና ላውንደሪ
* Front office service እንግዳ አቀባበል
* Tour Guide ቱር ጋይድ
* Tour Operation ቱር ኦፕሬሽን
* Baker and pastry production የዳቦና ኬክ ዝግጅት
* Culinary art የምግብ ዝግጅት





# ለኢንስቲትዩቱ የተሰጠውን ተልዕኮ የሚፈጽም ተግባር ተከናወነ።

ቱ .ኢ .ማ

ታህሳስ 20/2014 ዓ.ም

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከተሰጡት ተልዕኮች አንዱ የማማከር አገልግሎት ሲሆን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙ የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ሙያዊ ድጋፍ፣ የማማከር አገልግሎት እና የስራ ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ነው።

የቡድኑ ተግባር በዘርፉ እየተሰጠ ያለውን አገልግሎት ማሻሻል እና በክልሎቹ ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች፣ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ማህበራት እንዲሁም የስራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት ጋር የስራ ትስስር መፍጠር ነው።

ይህንን ተግባር እንዲያከናውን የተቋቋመው ከመምህራን የተውጣጣ ስድስት ቡድን ወደ ዘጠኝ ከተሞች በመጓዝ ሀዋሳና ወላይታ፣ አርባምንጭ፣ ኮንሶ ፣ ጅንካና ቱርሚ ፣ ድሬዳዋ፣ ሀረሪ እና ጅማ ከተሞች በመጓዝ በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፎች ለሚሰሩ ባለሙያዎች የሥራ ላይ ስልጠና እንደሰጡ የየቡድኑ ሪፖርት አቅራቢዎች ተናግረዋል፡፡

በክልሎቹ ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች፣ የሆቴልና ቱሪዝም ቢሮዎችና ዘርፍ ማህበራት እንዲሁም የስራ ዕድል ፈጠራ ተቋማት ጋር የስራ ትስስር ፈጥረው እንደመጡም ተገልጿል፡፡


ቡድኑ ሪፖርቱን በሚያቀርብበት ጊዜ የተገኙት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት እንደገለጹት በአጭር ጊዜ እንደዚህ አይነት ስራ መሠራቱ እና ኢንስቲትዩቱ የተሰጠውን ተልዕኮ በተግባር መፈፀሙ የሚያስመሰግን ሥራ መሆኑን ተናግረዋል።

ይህ በመረጃ የተደገፈው የቡድን ሥራ በአፋጣኝ ወደ ተግባር መግባት እንዳለበትና ከተቋማት ጋር የተደረገው አብሮ የመስራት ፍላጎት ህጋዊ ወደ ሆነ የስምምነት ምዕራፍ ማሸጋገር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።









## “ሀገር የሁሉም ናት "

"ሀገር ችግር ውስጥ ስትገባ እኛም ችግር ላይ መውደቃችን ነው"

"በሁለም መስክ ማድረግ የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ደግሞ ዝግጁ ነን"

ይህን የተናገሩት የገነት ሆቴልና የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰራተኞችና ሰልጣኞች ናቸው።

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት፣ የስራና ክህሎት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማቱ በሰሜን ሸዋ ዞን ደብረ ብርሃን ከተማ ተገኝተው ካደረጉት የቁሳቁስ፣ የስንቅና የገንዘብ ድጋፍ ባሻገር ዛሬም የማስልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች እና የገነት ሆቴል ባለሙያዎች ጥምረት በታው ድረስ ሄደው ለመከላከያ ሰራዊት አባላት በጊዜያዊ ማረፊያ ሥፍራ እና በደብረ ብርሃን ከተማ ሆስፒታል የሚገኙ በጦርነቱ ሰቢያ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖቻችንን የምሳና የእራት ፕሮግራም በማዘጋጀት ምገባ አካሂዷል።

በእራት ፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ሙፈሪያት ካሚል እና ሚኒስትር ዴኤታዎች እንዲሁም የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ሲሆኑ ለመከላከያ ሰራዊት አባላቱ ክብርት ሙፈሪያት ካሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

በመልዕክታቸውም የእናንተን ውለታ በገንዘብ፣ በቁስ መተካት አይቻልም ውድ ህይወታችሁን እየሰጣችሁ በጀግንነት ሀገር የምታቆዩ ናችሁ፤ ነገር ግን አለን፣ አይዟችሁ፣ በርቱ ብለን ደጀን ለመሆንና ምስጋና ለማቅረብ ነው እዚህ የተገኘነው ብለዋል። በዞኑ የመከላከያ ሰራዊት አስተባባሪ ሌ/ኮሎኔል አብዲ ሙሳ እና ኮሎኔል ዶ/ር ዓለሙም እየተደረገ ላለው ድጋፍ እና አጋርነት ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ክብርት ሚኒስትር አክለውም በሁሉም መስክ ድጋፋችን አሁንም ይቀጥላል፤ ሀገር ወደፊት ትቀጥላለች እጃችንን እየጠመዘዙ እንደፈለገን እናድርጋችሁ የሚሉንን የውጭ ሀይሎች ደግሞ ባለን የሰው ሃይል ተጠቅመን ድህነታችንን አሸንፈን በኢኮኖሚ ቀና እንድንል በርካታ የሥራ ዕድሎችን የምትፈጥር ሀገር እንድትኖረን አጥብቀን እንሰራለን ብለዋል። በተጨማሪም በተቋማችን ሰራተኞችና ተማሪዎች የተዘጋጀው ቋንጣ ለመከላከያ ሠራዊታችን እንዲደርስ ክብርት ሙፈሪያት ካሚል የሥራና ክህሎት ሚንስትር እና አመራሮች ለደብረብርሐን ከተማ አስተዳደር አስረክበዋል።

የምግብ ዝግጅቱ ላይ የተሳተፉ ሰልጣኞች የተቋሙ ሰራተኞችና የገነት ሆቴል ባለሙያዎች በበኩላቸው ስለ ዝግጅቱ ሲጠየቁ የምንሰራው ለሀገሩ ክብር ለሚዋደቀው የመከላከያ ሰራዊታችን በመሆኑ ደስተኞች ነን፣ ሀገር የወታደር ብቻ አይደለችም፤ የሁሉም ናት፤ ሀገር ችግር ውስጥ ስትሆን ደግሞ አያገባኝም ማለት አንችልም፤ እስካሁን የተደረጉት ዝግጅቶች ላይም በደስታ መሳተፋቸውን ገልጸዋል።

በመጨረሻም የብሔራዊ ቲያትር የባህል ሙዚቃ ቡድን አንጋፋና ወጣት ድምፃውያን የመከላከያ ሰራዊቱን አዝናንተዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማቱ እስካሁን ከ25 ሚሊየን ብር በላይ የሚገመት ድጋፍ አድርገዋል።

# ልጆቻችሁ የምትነግሩት ታሪክ ሰርታችኋል"



ለልጆቻችሁ የምትነግሩት ታሪክ ሰርታችኋል"
ይህን የተናገሩት ክብርት ሙፈሪያት ካሚል ናቸው።
የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት ለመከላከያ ሠራዊታችን እና በጦርነቱ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ፣ በሆስፒታል ለሚገኙ ህሙማን የሚሆን አልባሳት፣ የታሸጉ ምግቦች ፣ ፍራሽ ቆሎ፣ ዳቦቆሎና ኩኪስ በስጦታ አበርክተዋል።
ስጦታውን የተረከቡት የአፋር ዞን አምስት ወረዳ ሀደሌኤላ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ አደም ሄንኬብ እንደተናገሩት በአካባቢው የገባው አሸባሪ ቡድን በጭፍራ እና ካሳጊታ ያልተሳካለትን የጅቡቲን መንገድ የመያዝ ሴራ ወደ አዋሽና ገዋኔ በሚያወጣው ወረዳ ሙከራ አድርጎ እንደለመደው ሴቶችና ህፃናት ላይ ጉዳት ከማድረሱ በፊት በአካባቢው ነዋሪ ልዩ ሀይልና የመከላከያ ሰራዊቱ በሌሉበት ብቻቸውን በጀግንነት ተዋግተው ፤ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች መሆናቸውን ማስመስከራቸውን ተናግረዋል።
በጉብኝቱ እና በስጦታ መርሃ ግብሩ የተገኙት ክብርት ሙፈሪያት ካሚል አፋር ወራሪ ኃይሉ ከባድ መሣሪያ ይዞ የመጣውን ወራሪ ተዋግታችሁ በማሸነፋችሁ ለልጆቻችሁ የምትነግሩት አኩሪ ታሪክ ሰርታችኋል ፤ ኢትዮጵያውያንን አኩርታችኋልና ክብር ይገባችኋል ሲሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።
ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በመተባበር በአላጌ የግብርና ማሰልጠኛ ኮሌጅ ማገገሚያ ማዕከል ለሚገኙ የመከላከያ ሠራዊት አባላት የምሳ ግብዣ እና የደረቅ ምግቦች ስጦታ ማበርከቱ ይታወሳል።





ሶስተኛ ዓመት የቱሪዝም ተማሪዎች በመልካ ቁንጥሬና በጢያ ትክል ድንጋይ የተግባር ስልጠና አደረጉ፡፡
ቱ. ማ .ኢ. ህዳር 27/2014 ዓ. ም
በመልካ ቁንጥሬ ታሪካዊ በታ ጥንታዊ የሰው ልጆች ለሥራ ይጠቀሙበት የነበረ በርካታ ከድንጋይ የተሰሩ መሳሪዎችና የእንስሳት ስብስብ የተገኙበት በታ እንደሆነና በታውም በ1965 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንደተጠና አስጎብኚው ገልጸዋል፡፡ የጥናቱ ውጤትም ሥፍራው ከስምንት መቶ ሺህ ዓመት በላይ የሰው ልጆች መኖሪያ ሆኖ ያገለግል እንደነበረ የሚያመለክት ሲሆን ሥፍራውን ከሌሎች ለየት የሚያደርገው የሰው ልጆች በህይወት ሂደት ቀጥ ብለው ለመራመድ የጀመሩበት ፣ ድንጋይን ከድንጋይ በማጋጨት እሳትን የፈጠሩበት ፣ ቤተሰባዊ አኗኗርን የጀመሩበት ረዥም እድሜ የኖሩ የሰው ልጆች ቅሪተ አካል በመገኘቱ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

ሌላው ጢያ ትክል ድንጋይ ነው፡፡

* ጢያ ትክል ድንጋይ በ1972 ዓ ም በዓለም ቅርስነት ተመዝግቧል ።
* ትክል ድንጋዩ ትንሹ አንድ ሜትር ሲሆን ትልቁ አምስት ሜትር ነው፡፡
* በድንጋይ ተቀርጸው የሚታዩት ምስሎች አምስት ናቸው ። እነሱም

1, ሳንጃ ምስል
2, የከበሮ ምስል
3, የሴት ምስል
4, የጋሻ ምስል እና
5, የወንድ ብልት ምስል መሆናቸውን የመስህቡ አስጎብኚ አቶ ሲሳይ ዋቅጅራ ገልጸዋል ።

በዚህ የተግባር ስልጠና የተሳተፉ ሰልጣኞች ለቀጣይ ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ለስራ ዕድል ፈጠራ እንዲያመቻቸው ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ እንደሆነ የቱሪዝም መምህር








# የባህል ቀን" አከባበር ፤

የተቋማችን ሰልጣኞች በብሔር ብሔረሰቦች ሙዚቃ ታጅበው አክብረዋል።
ታህሳስ 1/2014ዓ.ም



የባህል ቀን እኛ የሆቴልና ቱሪዝም ሰልጣኞች ሁላችንም ከተለያየ አካባቢ የተሰባሰብን በመሆናችን የተለያየ ባህል ያለን ሰልጣኞች ነን ይህን ቀን በማክበር እርስ በርስ ትውውቅ እንድናደርግ ይረዳናል ብሏል የ3ኛ ዓመት የምግብ ዝግጅት ሰልጣኝ ክሊንተን መስፍን። ሰልጣኞቹ የተለያዩ የብሔር ብሔረሰብ አልባሳትን ለብሰው ፣ ባህላዊ ጨዋታውንም በመጫወት በዓሉን አክብረዋል።

# "የጥቅም ግጭትን ለመከላከል ሙስናን መጸየፍ "

ቱ ማ ኢ ህዳር 30/2014 ዓ.ም

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ18ኛ ጊዜ በሀገር አቀፍ ለ17ኛ ጊዜ የሚከበረው የሙስና ቀን በተቋማችን ተከበረ። የተቋማችን የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት አቶ ታምራት ተፈራ እንደገለጸው በሀገራችን ለ17ኛ ጊዜ ሙስና ቀን ቢከበርም የሚፈለገው ለውጥ አላመጣም፤ ሆኖም ዘንድሮ በስነ -ምግባር የታነፀ አመራር ከሙስና ለፀዳች ኢትዮጵያ በሚል በስፋት እየተከበረ እንደሆነና ይህንን በአመራር የተጀመረው ለውጥ ወደ ሁሉም እንዲደርስ ርብርብ በማድረግ ሙስናን መቀነስ እንደሚቻል ተናግሯል። በውይይቱ የተገኙት ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት እንደተናገሩት በሀገራችን የጥቅም ግጭትን ለመከላከል በቅድሚያ ሙስናን መፀየፍ አለብን ብለዋል። ይህም የሀገራችንን እድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደሚፈለገው ለውጥ እንዳናሳይና በተለያዩ ጥቅሞች እንዲንጋጭ ምክንያት ሆኗል። ስለሆነም በስነ-ምግባር የታነፀ ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ በመፍጠር ሙስና ከመፈጠሩ በፊት በመከላከል ላይ በማተኮር ለሀገር ለውጥ መታገል እንዳለብን አሳስበዋል።



